ጤናሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
Ministry of Health - Ethiopia
የዜጎችጤናለሀገርብልጽግና!
Healthier Citizens for Prosperous Nation

የጤና ሚኒስቴር

የውጭ አገር የሕክምና አገልግሎት ቅብብሎሽ ሥርዓት ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1128/2018

መጋቢት 2018

አዲስ አበባ

<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የጤና ሚኒስቴር</u>
<u>መመሪያ ቁጥር 1128/2018</u>

የውጭ አገር የሕክምና አገልግሎት ቅብብሎሽ ሥርዓት ማስፈፀሚያ መመሪያ

ለሕክምና ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ኢትዮጵያዊ ጤንነቱ፤ደህንነቱ እና ክብሩ ተጠብቆ ከፍተኛ ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል የሕግ ማእቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሀገር አቀፍ ደረጃ የውጭአገር የሕክምና ቅብብሎሽን ወጥ የሆነ አተገባበር ስርዓት በመዘርጋት አላስፈላጊ የታካሚን እንግልት መቀነስ፣ለህክምናው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በተሟላ መልኩ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የውጭ አገር ሕክምና አገልግሎት የሚያስፈልገውን ተገልጋይ ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ከውጭ ሕክምና ተቋም ጋር የሚያገናኝ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የጤና ሚኒስቴር የጤና አገልግሎት አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 **አንቀጽ** 11 (3) **እና አንቀፅ** 58(2)**መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡**

Habtamu Hailemeskel

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የውጭ አገር ሕክምና አገልግሎት ቅብብሎሽ መመሪያ ቁጥር 1128/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"ሆስፒታል" ማለት** በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ወይም ከዛ በላይ ደረጃ የተሰጠው ሆስፒታል ወይም ኮምፕርሄንሲቭ ሆስፒታል በሌለባቸው ክልሎች፤ በቢሮው የተመረጠ አጠቃላይ ሆስፒታል ሆኖ የውጪ አገር ሕክምና ቅብብሎሽ ማስረጃ መስጠት የሚችል ተቋም ነው፡፡

2/ **"ታካሚ"** ማለት በቦርድ ማስረጃ መሰረት የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ውጭ ሀገር የሚሄድ ግለሰብ ነው፤

3/ **"ታካሚውን የተከታተለው ሀኪም"** ማለት ታካሚው ከሚታከመው የህመም ዓይነት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ትምህርት የተማረ ስፔሻሊስት ወይም ሰብስፔሻሊስት ነው፤

4/ **"የውጭ አገር የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ቅብብሎሽ"** ማለት ታካሚ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ሚኒስቴሩ ከሀገር ውስጥ የጤና ተቋም ወደ ውጭ አገር የሚገኝ የጤና ተቋም የሚያሸጋግርበት ስርዓት ነው፤

5/ **"ቦርድ"** ማለት በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተርየተቋቋመ አደረጃጀት ሆኖ ታካሚ ወደ ውጭ አገር ሄዶ መታከም እንዳለበት የሚገልፅ የሕክምና ማስረጃ የሚሰጥ አካል ነው፤

6/ **"የቦርድ ማስረጃ"** ማለት ታካሚው ወደ ውጭ አገር ሄዶ መታከም እንዳለበት የሚገልጽ በቦርድ የተሰጠ የሕክምና ሰነድ ነው፤

7/ **"የፈቃድ ሰርተፍኬት"** ማለት በቀረበው የቦርድ ማስረጃ መሰረት ታካሚው ወደ ውጭ አገር ሄዶ እንዲታከም በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ሰነድ ነው፡፡

8/ **"ወኪል"** ማለት የዉጭ አገር ህክምና አገልግሎት የሚያስፈልገዉን ታካሚ ወደ ዉጪ የሚልክ ወይም ከዉጪ ህክምና ተቋም ጋር የሚያገናኝ ተቋም ሆኖ ይህንን ተግባር እንዲያከናውን ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤

9/ **"ቢሮ"** ማለት የውጭ አገር ህክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ሥርዓት መተግበርን የሚያረጋግጥ የክልል ጤና ቢሮ ወይም በህግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም ነው፤

10/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፕብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

11/ **"አዋጅ"** ማለት የጤና አገልግሎት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 ነዉ፤

12/ በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

13/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አገላለፅ የሴት ፆታን ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የውጭ አገር የሕክምና አገልግሎት ቅብብሎሽ ሥርዓትን ለማስፈፀም በሚከናወን ተግባራት እና ይህንኑ ተግባራት በሚያከናውን ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የውጭ አገር የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ቅብብሎሽ</u>

4. <u>ለውጭ አገር ህክምና የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

1) ማንኛውም ታካሚ ያጋጠመው የጤና ችግር ከሐገሪቱ የጤና አገልግሎት ደረጃ በላይ ከሆነ ከሐገር ውጭ እንዲታከም በህክምና ቦርድ የጸደቀ የህክምና ማስረጃ እና ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2) ማንኛዉም ታካሚ የዉጭ ሀገር ሕክምና ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ማግኘት የሚችለው፡-

ሀ) ሕክምናው በሀገር ውስጥ ሊሰጥ የማይችል ከሆነ (የህክምና መመርመሪያ መሳሪያው ከሌለ፣ የህክምና አገልግሎቱን መስጠት የሚችል ባለሙያ ከሌለ) ወይም ለምርመራ የናሙና ዝውውር የማይቻል መሆኑ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ፤

ለ) የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም የሕክምና አገልግሎቱን በሀገር ውስጥ ለማግኘት በረጅም ወረፋ ምክንያት ጊዜ የሚወስድ ሲሆን እና ታካሚው አገልግሎቱን ሳይወስድ መቆየቱ በጤናው ላይ የማይመለስ ጉዳት ወይም ሞት እንደሚደርስ በቦርዱ ሲረጋገጥ፤ወይም

ሐ) በውጭ ሀገር ለተሰጠ የህክምና አገልግሎት ታካሚው የህክምና የክትትል ቀጠሮ እንዳለው ከታከመበት የጤና ተቋም ማሰረጃ ካቀረበ እና በቦርዱ ለክትትል መሄዱ ተገቢ ነዉ ተብሎ ሲወሰን ነው።

5. <u>የውጭ አገር ህክምና አገልግሎት ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ማስረጃዎች</u>

1/ በውጭ አገር የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ የሚጠይቅ ታካሚ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ወይም የኢትዮጵያ ፓስፖርት፤

ለ) ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ማንነቱን የሚገልጽ የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ወይም የልደት ምስክር ወረቀት፤

ሐ)ስድስት ወር ያላለፈው የተሟላ የቦርድ ማስረጃ፤

መ) የባንክ ሂሳቡ ውስጥ ቢያንስ 500,000 ብር መኖሩን በባንክ የተረጋገጠ ሰነድ፤እና

ሠ) ለአገልግሎት የተከፈለበት ሰነድ፤

2/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ፊደል ተራ (ሀ)- (ሠ) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ለንቅለ ተከላ ህክምና የሚከተሉትን ሰነዶችን አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) በሚመለከተው አካል በተቀባይ እና በለጋሽ መካከል የተዋዋሉበት የሰነድ ማስረጃ፤

ለ) የለጋሽ የጤና ምርመራ ማስረጃ፤እና

ሐ) የባንክ አካውንቱ ውስጥ ቢያንስ 1,000,000 ብር መኖሩን በባንክ የተረጋገጠ ሰነድ፤

3/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ፊደል ተራ (መ) እና ንኡስ አንቀፅ (2) ፊደል ተራ (ሐ) ድንጋጌዎች ቢኖርም ለህክምና የሚያስፈልገው ወጪ፡-

ሀ) በሚሰራበት ተቋም በኩል የሚሸፈን ከሆነ ተቋሙ የሕክምና ወጪውን የሚሸፍን ስለመሆኑ ለሚኒስቴሩ የተፃፈ ደብዳቤ ፤

ለ) በውጭ አገር በሚኖር ሰው የሚሸፈን ከሆነ ለታካሚው የተላከ ቪዛ፤

ሐ) በውጭ አገር በሚገኝ ህጋዊ ድርጅት በኩል የሚሸፈን ስለመሆኑ ለሚኒስቴሩ የተፃፈ ደብዳቤ ፤ወይም

መ) በሀገር ውስጥ በሚገኝ መንግስታዊ ወይም ህጋዊ በሆነ ድርጅት በኩል የሚሸፈን ስለመሆኑ ለሚኒስቴሩ የተፃፈ ደብዳቤ፤

ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ ከሚኒስቴሩ የተሰጠው የፈቃድ ሰርተፍኬት ሰነድ የሚያገለግለው ለ ስድስት ወር ብቻ ነው፡፡

5/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ታካሚው ከሚኒስቴሩ በተሰጠው ፈቃድ መሰረት ወደ ዉጭ ሀገር ሄዶ ሳይታከም ስድስት (6) ወር ያለፈ እንደሆነ የሚከተሉትን ሰነዶችን በማሟላት ፈቃዱ እንዲታደስለት ሊጠይቅ ይችላል፡-

ሀ) በሚኒስቴሩ የተሰጠው ስድስት ወር ያለፈው የፈቃድ ሰርተፍኬት ሰነድ፤

ለ) በሚኒስቴሩ የተሰጠውን የፈቃድ ሰርተፍኬት ሰነድ ሳይጠቀሙበት ከስድስት ወር በላይ የሆነበትን ምክንያት ህጋዊ ማስረጃ፤

ሐ) የታደሰ የቦርድ ማስረጃ ሰነድ፤እና

መ) ከባንክ የውጭ ምንዛሬ ላለመወሰዱ የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

6/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ለታካሚው ከሚኒስቴሩ የተሰጠው የፈቃድ ሰርተፍኬት ሰነድ የጠፋ እንደሆነ ሰነዱ የጠፋ ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ ከፖሊስ ማስረጃ በማቅረብ ምትክ የፈቃድ ሰርተፍኬት ማግኘት ይችላል፡፡

6. <u>ስለታካሚ አስታማሚ</u>

1/ ቦርዱ በውጭ አገር እንዲታከም ከተፈቀደለት ታካሚ ጋር የሚሄድ አንድ አስታማሚ መፍቀድ አለበት፡፡

2/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም እንደ የነገሩ ሁኔታ የታካሚውን የጤና ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቦርዱ እስከ ሁለት አስታማሚ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም እድሜው ከ 18 ዓመት በታች ለሆነ ታካሚ ወላጆች ወይም በሕግ ሞግዚትነት የተሰጠው ግለሰብ አስታማሚ ሆኖ አብሮ መሄድ አለበት፡፡

4/ ከታካሚው ጋር አብሮ እንዲሄድ የተፈቀደለት አስታማሚ ከታካሚው ጋር አብሮ መሄድ አለመቻሉን የሚያስረዳ አሳማኝ የሆነ ማስረጃ ከሚመለከተው ህጋዊ ተቋም ከቀረበ ሚኒስቴሩ አስታማሚው እንዲቀየር ሊፈቅድ ይችላል፡፡

Habtamu Hailemeskel

ክፍል ሶስት

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ እና መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች

1/ ማንኛውም ሰው ወኪል ሆኖ ለመስራት ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ለጤና ባለሙያ ለሆነ ሰው ነው፡፡

3/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ለዚሁ ዓላማ ሲባል የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ማስረጃዎች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የአመልካቹን ማንነት እና አድራሻ የሚገልፅ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ወይም ፓስፖርት፤

ለ) አመልካች የጤና ባለሙያ ስለመሆኑ የሚያሳይ የታደሰ የሙያ ፈቃድ፤

ሐ) የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ሰነድ፤

መ) በውጭ አገር የሚገኘው የጤና ተቋም የሥራ ፍቃድ ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የተረጋገጠ ማስረጃ ሰነድ፤

ሠ) ለታካሚው በውጭ አገር የህክምና አገልግሎት የሚሰጠው የጤና ተቋም በሀገር ውስጥ የተመዘገበ ህጋዊ ወኪል ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ፤

ረ) በውጭ አገር የሚገኘው የጤና ተቋም ለሚሰጠው አገልግሎት በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የተረጋገጠ አለም ዓቀፍ የጥራት ሰርተፊኬት ማረጋገጫ ሠነድ ወይም ሀገር አቀፍ የጥራት ሰርተፊኬት ማረጋገጫ ሠነድ፤እና

ሰ)የውጭ አገር ህክምና ቅብብሎሽ በተመለከተ ከሚኒስቴሩ ጋር የተፈራረመው የውል ስምምነት ሰነድ፡፡

4/ ሚኒስቴሩ ማመልከቻ በቀረበለት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ መስፈርቶቹ መሟላታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፤ የቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ ካደረገ ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ መግለጽ እና ቅሬታ ካለው እንደገና እንዲታይለት ለመጠየቅ መብት እንዳለው ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ ወኪሉ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሥራ ቦታው በሚታይ ቦታ ላይ

ማስቀመጥ አለበት፡፡

8. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዘት</u>

ለወኪል የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በዚህ መመሪያ እገዘል-4 መሰረት ይሆናል፡

9. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማደስ</u>

1/ማንኛውም ወኪል የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በየዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

2/ ማንኛውም ወኪል የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ አንድ ወር በፊት ለሚኒስቴሩ የእድሳት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

3/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ወኪል ለዚሁ ዓላማ ሲባል የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ማስረጃዎች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ/ የአመልካቹን ማንነት እና አድራሻ የሚገልፅ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፋይዳ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት፤

ለ/ ለእድሳት የሚጠየቀውን የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ሰነድ፤

ሐ/ ከዚህ ቀደም የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፤እና

መ/ የውጭ አገር ህክምና ቅብብሎሽ በተመለከተ ከሚኒስቴሩ ጋር የተፈረመው የውል ስምምነት ሰነድ፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) ስር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካላሳደሰ አግባብ ባለው ሕግ የተቀመጠውን ቅጣት በመክፈል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ይታደስለታል፡፡

10. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማሻሻል</u>

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚከተሉት ምክንያቶች ይሻሻላል፡-

1/ ወኪሉ ወይም በውጭ አገር የሚገኘው የጤና ተቋሙ የሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት ዝርዝር ላይ ለውጥ አድርጎ ከሆነ፤ወይም

2/ የውጭ አገር ህክምና ቅብብሎሽ በተመለከተ ከሚኒስቴሩ ጋር የተፈረመው የውል ስምምነት ሰነድ ማሻሻያ ከተደረገበት፡፡

11. <u>ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

1/ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ወይም

የተቃጠለበት ወኪል ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡

2/ ማንኛውም ወኪል ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትየተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን መመለስ፤

ለ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የጠፋ ወይም የተቃጠለ ከሆነ የጠፋ ወይም የተቃጠለ መሆኑን ከፍትህ አካል ማረጋገጫ ሰነድ ማምጣት፤ እና

ሐ) የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፡፡

3/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) መሰረት የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ላሟላ ወኪል ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

ክፍል አራት
ስለ ቦርድ

12. የቦርድ አመሰራረት

1/ ቦርዱ በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ይቋቋማል፡፡

2/ የቦርዱ አባላት የሙያ ስብጥርን፤የስራ ልምድን፣ የሙያ ስነ- ምግባርን እና የስፔሻሊቲ ወይም የሰብስፔሻሊቲ ደረጃ መስፈርቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ ይሆናል፡፡

3/ የቦርዱ የአባላት ቁጥር ከ3 ያላነሰ ከ 5 ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

4/ የቦርዱ ሰብሳቢ በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ይመረጣል፡፡

5/ ቦርዱ በሳምንት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከአባላቱ አንድ ሶስተኛው ስብሰባ እንዲካሄድ ሲጠይቁ በማንኛውም ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

6/ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

7/ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፤ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሀሳብ የኮሚቴ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

8/ ሆስፒታሉ የቦርዱ የአሰራር ስርዓት፣የቦርድ አባላት የስራ ዘመን፤እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ይህንን መመሪያ መሰረት አደርጎ ግልፅ በሆነ መንገድ የመተዳደርያ ደንብ ያዘጋጃል፡፡

13. ከቦርድ አባልነት ስለ መነሳት

አንድ የቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊነሳ ይችላል፡-

1/ የጥቅም ግጭት ሲኖር፤

2/ የጤና እክል ወይም፣ የስነ-ምግባር ጉድለት ሲያጋጥም፤

3/ በወንጀል ተከሶ ከተፈረደበት፤

Habtamu Hailemeskel

4/ ከሚሰራበት ተቋም ከለቀቀ፤ወይም

5/ ያለምንም ፈቃድ ወይም አስቀድሞ ባለማሳወቅ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ የቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎች ላይ ቀሪ ሲሆን እና በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ሳያሻሽል ሲቀር፡፡

14. <u>የጥቅም ግጭት ስለማስተዳደር</u>

ማንኛውም የቦርድ አባል በቦርድ ዉስጥ ካለው ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጥቅም ግጭት ሲያጋጥመው ይህንኑ ለኮሚቴው በማሳወቅ ጉዳዩ ከሚታይባቸው የቦርዱ ስብሰባዎች ሁሉ ራሱን ማግለል አለበት፡፡

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>የሚመለከተው አካል ተግባርና ኃላፊነት</u>

15. <u>የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነቶች</u>

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1/ ከሆስፒታል እና ከቢሮ የተላከውን የቦርድ ማስረጃ ያረጋግጣል፣ያጸድቃል፤
2/የውጭ ሀገር ሕክምና ቅብብሎሽ የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋል፤ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤
3/ለውጪ ሀገር ሕክምና ቅብብሎሽ ማስፈፀሚያነት የሚውል ቅጾችን ያዘጋጃል፤ ለሚመለከታቸው ሆስፒታሎች ያሰራጫል፣
4/የቦርድ ማስረጃውን መሰረት በማድረግ ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ለመታከም በዚህ መመሪያ እዝል-2 እና እዝል-3 መሰረት የፈቃድ ሰርተፍኬትይሰጣል፤
5/በዚህ መመሪያ መሰረት ለወኪሉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ያድሳል፤ያግዳል፤ ይሰርዛል፤
6/ በውጭ ሀገር የህክምና አገልግሎት የሚሰጠውን የጤና ተቋም እንዳስፈላጊነቱ ያለበትን ሁኔታ በአካልበመገኘት ያረጋግጣል፤
7/የብሄራዊ የሕክምና አገልግሎት መዘርዝር መረጃ ቋት ያዘጋጃል፤ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ያደርጋል፤
8/ ከውጭ አገር ሕክምና የፈቃድ ሰርተፍኬት አሰጣጥ ጋር የተገናኙ ሌሎች ተያያዥ ተግባራትንም ያከናውናል፡፡

16. <u>ታካሚውን የተከታተለው ሀኪም ተግባር እና ሀላፊነት</u>

ታካሚውን የተከታተለው ሀኪም፡-

1/ ህክምናው በሀገር ውስጥ ሊሰጥ እንደማይችል እና ህመሙ ሀገር ውስጥ መታከም የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

2/ ወደ ውጭ አገር ሄዶ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ የተፈለገበት አግባብ እና የሕክምናው ውጤት ማስረጃ ለታካሚው ማሳወቅ አለበት፤

3/ ታካሚው በውጭ አገር ህክምና ለማግኘት መስማማቱን የሚገልጽ የስምምነት ቅጽ ማስሞላት እና ማስፈረም አለበት፤

4/ የታካሚውን የተሟላ መረጃ በ 3 የስራ ቀናት ውስጥ ለቦርድ መስጠት አለበት፡፡

17. ስለ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

ቦርዱ የውጭ ሀገር ሕክምና ቅብብሎሽ በተመለከተ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1/ የታካሚው የሕክምና ማስረጃ ታካሚውን ከተከታተለው ሀኪም በደረሰው በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፤

2/ ቦርዱ የወሰነውን ውሳኔ ለሜዲካል ዳይሬክተሩ በ 03 የሥራ ቀን ውስጥ ለማጸደቅ መላክ አለበት፤

3/በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) መሰረት ለሜዲካል ዳይሬክተሩ የተላከው ማስረጃ በዚህ መመሪያ እዝል-1 መሰረት ከ 3 ባላነሰ የቦርድ አባላት የተፈረመ መሆን አለበት፡፡

18. የቦርድ ማስረጃ ስለሚያረጋግጥ ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ለቢሮው ወይም ለሚኒስቴሩ የላከውን የቦርድ ማስረጃ የሚያረጋግጥ ባለሙያ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1/ ለታካሚው የቦርድ ማስረጃ የሰጠው ሆስፒታል አገልግሎቱን መስጠት የማይችል መሆኑን ያረጋግጣል፤

2/ የቦርድ ማስረጃ የተሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

3/የቦርድ ማስረጃ በተዘጋጀው ቅፅ መሰረት በሚመለከተው ባለሙያ የተሞላ እና ስምና ፊርማዎቹ ትክክለኛ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

19. የሜዲካል ዳይሬክተር ተግባርና ኃላፊነት

ሜዲካል ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1/ በዚህ አንቀፅ 17 (3) መሰረት የቀረበለት የሕክምና ማስረጃ የተሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) መሰረት ያረጋገጠውን ማስረጃ ያፀድቃል፤

3/ የፀደቀውን የቦርድ ማስረጃ ለሚኒስቴሩ ወይም ለቢሮው በ 03 የስራ ቀን ውስጥ ይልካል፡፡

Habtamu Hailemeskel

20. <u>የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት</u>

ቢሮው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-
1/ በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ፀድቆ የተላከውን የቦርድ ማስረጃ ያረጋግጣል፣ያጸድቃል፤

2/ የጸደቀውን የቦርድ ማስረጃ ወደ ሚኒስቴሩ ይልካል፤

3/ አገልግሎቱን ዲጂታላይዝ ለማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

4/ የመረጃ አያያዝ ስርዓትን ያጠናክራል፣ ያዘምናል፡፡

21. <u>የሆስፒታል ተግባርና ኃላፊነት</u>

ሆስፒታሉ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1/ የውጪ አገር ሕክምና ቅብብሎሽ የቦርድ ማስረጃ መስጠት የሚችለው በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ወይም ከዛ በላይ ደረጃ የተሰጠው ሆስፒታል ወይም ኮምፕርሄንሲቭ ሆስፒታል በሌለባቸው ክልሎች በቢሮው የተመረጠ አጠቃላይ ሆስፒታል ነው፤
2/ በስራ ላይ ያሉ የቦርድ አባላት ስምና የፊርማ ናሙና ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ወይም ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፤
3/ የቦርድ ማስረጃው በተቋሙ ቦርድ የተረጋገጠ መሆኑን ማጣራት አለበት፤

4/ ሜዲካል ዳይሬክተሩ የቦርዱ ሰነድ ለሚኒስቴሩ ወይም ለቢሮው መላኩን ያረጋግጣል፤
5/ የተቀየሩ የቦርድ አባላት ስም ዝርዝር ለሚኒስቴሩ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፤

6/ በሚኒስቴሩ የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶችን መከተል እና መተግበር አለበት፡፡

22. <u>የወኪል ተግባርና ኃላፊነት</u>

ወኪሉ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1/ ስለ ውጭ አገር ስለሚገኘው የጤና ተቋም በሚኒስቴሩ የሚጠየቀውን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤
2/ታካሚው ለህክምና በሄደበት ሀገር ውስጥ ለህክምና አገልግሎት እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ በሆስፒታል ውስጥም ሆነ ከሆስፒታል ውጭ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት፤
3/ታካሚውን የተቀበለው የጤና ተቋም በማንኛውም ምክንያት ህክምናውን ለመስጠት ፈቃደኛ በማይሆንበት ጊዜ ወኪሉ ከሆስፒታሉ የተላከውን ማሳወቂያ በደረሰው በአንድ የስራ ቀን ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፤
4/ሚኒስቴሩ የታካሚውን የሕክምና ሪከርድ ጋር በተያያዘ መረጃ ከጠየቀ ወኪሉ ይህንኑ መረጃ

ማቅረብ አለበት፤

5/ለታካሚው ስለተሰጠው የሕክምና አገልግሎት በተመለከተ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ በየሩብ ዓመቱ ማቅረብ አለበት፤

6/ ውጭ አገር የሚገኘው የጤና ተቋም ለሚሰጠዉ የህክምና አገልግሎት ለሚከሰት ጥራት ደረጃ ጉድለት፤የህክምና ስህተት፣ የሙያ ግድፈት እና መሰል ድርጊቶች ለታካሚው ካሳ መክፈል አለበት፡፡

ክፍል ስድስት

አስተዳደራዊ እርምጃ እና የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት

23. አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

ማንኛውም ወኪል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጥ፣ የሚያሳግድ ወይም የሚያሰርዝ ጥፋት ፈፅሞ ቢገኝ ሚኒስቴሩ እንደአግባብነቱ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

24. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት የሚያበቁ ጥፋቶች

ማንኛውም ወኪል ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንደ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ሚኒስቴሩ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይችላል፡-

1/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሥራ ቦታው በሚታይ ቦታ አለማስቀመጥ፤

2/ ወቅቱን የጠበቀ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት አለመላክ፤

3/ ከስራው ጋር በተያያዘ በሚኒስቴሩ የሚጠየቀውን ማስረጃ አለማቅረብ፤

4/ የውጭ አገር ሕክምና ቅብብሎሽ የሚመለከቱ አስፈላጊ ሰነዶችንና መረጃዎችን በአግባቡ አለመያዝ፤

5/ መዝገቦችን ለምርመራ (ኢንስፔክሽን) በተጠየቀ ጊዜ ፈቃደኛ አለመሆን፤

6/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 22 (2) መሰረት ለታካሚው አስፈላጊውን ድጋፍ ካላደረገ፤

7/ ለታካሚው በውጭ አገር ስለሚገኘው የጤና ተቋም የተጋነነ መረጃ ከሰጠ፤

8/ ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ ጥፋቶች ከፈፀመ፡፡

25. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማገድ የሚያበቁ ጥፋቶች

1/ ማንኛውም ወኪል ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንደ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊያግድ ይችላል፡-

ሀ)ሁለት ጊዜ ከስራው ትግበራው ጋር በተያያዘ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ተገቢውን ማስተካከያ ሳያደርግ ከቀረ፤

ለ) ፈቃድ ከተሰጠው ተግባር ውጪ ሲሰማራ ከተገኘ፤

ሐ) በወኪሉ ላይ የሚቀርብ ክስ ላይ ለሚኒስቴሩ ቀርቦ ውሳኔ እስከሚያገኝ፤

መ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 9(2) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላሳደሰ፤

ሠ) ለስረዛ የሚያበቁ ግድፈቶች ሲፈጠሩ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በሚኒስቴሩ ቀርቦ ውሳኔ እስከሚያገኝ፤ወይም

ረ) ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ ጥፋቶች ከፈፀመ፡፡

2/ ሚኒስቴሩ እንደአግባቡ ከ 6 ወር ላላነሰ ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊያግድ ይችላል፡፡

26. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመሰረዝ የሚያበቁ ጥፋቶች</u>

1/ማንኛውም ወኪል ከሚከተለት ምክንያቶች በአንደ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 25 ንኡስ አንቀፅ (2) የተጠቀሰውን የእገዳ ቅጣት ተላልፎ አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፤

ለ) በውጭ አገር የሚገኘው የጤና ተቋም ወይም ወኪሉ የሚሰጠው አገልግሎት ከተቋረጠ፤

ሐ) በውጭ አገር የሚገኘው የጤና ተቋም የሚሰጠው አገልግሎት ከስታንዳርድ በታች መሆን በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠ፤

መ) በውጭ አገር የሚገኘው የጤና ተቋም የውል ስምምነት እንዲቋረጥ ከጠየቀ፤

ሠ) ለታካሚው የተሰጠው የህክምና አገልግሎት ጥራት አለመኖሩ፤የህክምና ስህተት ወይም የሙያ ግድፈት መድረሱ ከተረጋገጠ፤

ረ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ሰ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ (4) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካላሳደሰ፤

ሸ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሽፋን አድርጎ ህገ ወጥ ተግባር ከፈጸመ ወይም በህገ ወጥ ተግባር ከተሳተፈ፤

ቀ) እገዳ ተጥሎበት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 25 ንኡስ አንቀፅ (2) መሠረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ፤

በ)በዚህ መመሪያ አንቀፅ 25 መሠረት እገዳ ተጥሎበት በአንድ አመት ውስጥ እገዳ ሊያስከትል የሚችል ሌላ ጥፋት ደግሞ የፈጸመ እንደሆነ፤

ተ)ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ ጥፋቶች ከፈፀመ፡፡

2/በወንጀል ሕጉ መሠረት ቅጣት ያልተቀጣ ካልሆነ በስተቀር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ሰው የምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘበት ቀን አንስቶ ከአንድ ዓመት በኋላ አዲስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የስረዛው ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) እና (መ) ላይ በተገለፀው ምክንያት ከሆነ በማንኛውም ጊዜ አዲስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡

27. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ</u>

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ወይም በራሱ ፈቃድ ስራውን ያቆመ ወኪል በአስር የስራ ቀናት ውስጥ የምስክር ወረቀቱን የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

28.<u>የቅሬታ አቀራርብና አፈታት ሥርዓት</u>

1/ ማንኛውም ሰዉ በዚህ መመሪያ መሰረት በተላለፈበት የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለአስተዳደር ተቋሙ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የተቋም የበላይ ኃላፊ ዉሳኔ መስጠት አለበት፡፡

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

29. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

1/ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ይሆንባቸዋል ተብለዉ በመመሪያው የተጠቀሱ አካላት በሙሉ ለመመሪያዉ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

2/ የዚህ መመሪያ ድንጋጌ ሲጥስ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

30. <u>ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ሀኃች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

31. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በጤና ሚኒስቴር ይፋዊ ድሕረ- ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ መጋቢት፣ 2018 ዓ.ም

መቅደስ ዳባ (ዶ/ር)

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር

እዝል-1

Abroad Referral Medical Board Certificate

Date_____

MRN_____

Full name of the patient _____Age _____Sex_____

Address: - Region _____zone_____ Woreda_____ kebele_____

Department----------

Meeting Date----------

Brief Medical history

_____
_____
_____

Physical Findings

_____
_____
_____

Investigations

_____
_____

Diagnosis

_____
_____

Treatment given

_____
_____

Reason for referral

_____
_____

Number of Attendant

_____

Approved Board members	**Signature**	**Date**
• Dr._____	_____	_____
• Dr._____	_____	_____
• Dr._____	_____	_____
• Dr._____	_____	_____
• Dr._____	_____	_____

CED/CCD Name _____ Signature_____Date_____

Requested date_____
Requested by_____

አዝል-2



Ministry of Health-Ethiopia

PERMISSION CERTIFICATE
For Abroad Medical Referral (Organ Transplant cases)
Certificate No.: _____
Date of Issue: _____
To: Immigration, Ethiopia Bank, Ministry of Foreign Affairs, Ethiopian Embassies, and All Concerned Bodies
This is to formally certify that:
Patient Full Name: _____
Age / Sex: _____ / _____
Passport Number: _____
Recommended Treatment: _____
Destination Hospital: _____
Destination Country: _____
Following a comprehensive assessment and approval by the certified medical board at the referring facility, the above-named patient has been **granted official permission** by the Federal Ministry of Health to seek medical care abroad for the above-mentioned condition, as the service is currently unavailable in Ethiopia.

In line with the medical board's recommendation, the patient will be accompanied by:

- **Donor Name:** _____
Relationship to Patient: _____
Passport/ID Number: _____

- **Attendant (if applicable):** _____

Supporting Documents Attached:

- Certified medical board referral from the referring hospital
- Affidavit and relationship confirmation, authenticated by the Documents Authentication and Registration Service

Purpose of This Certificate

This certificate is issued for the purpose of facilitating:

- Visa and passport facilitation (where applicable) and immigration clearance
- Currency approval and foreign exchange processing via Ethiopia Bank
- Coordination with the Ministry of Foreign Affairs and Embassies
- Admission and coordination with the overseas treating hospital

Important Notes

- This certificate is valid only for the patient and named companions above
- It is non-transferable and any alteration or misuse will render it void
- Valid until: Six Months from date of issue

The Federal Ministry of Health respectfully requests all relevant institutions to provide the necessary support and cooperation for the patient and companions during the treatment process.

Authorized by:
Name: _____
Title:
Organization: Ministry of Health, Ethiopia
Signature: _____
Official Seal
ቅጽል-3

እዝል-3

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

Ministry of Health-Ethiopia

PERMISSION CERTIFICATE

For Abroad Medical Referral (Other than Organ Transplant cases)

Certificate No.: _____

Date of Issue: _____

To: Immigration, Ethiopia Bank, Ministry of Foreign Affairs, Ethiopian Embassies, and All Concerned Bodies

This is to formally certify that:

Patient Full Name: _____

Age / Sex: _____ / _____

Passport Number: _____

Recommended Treatment: _____

Following a comprehensive assessment and approval by the certified medical board at the referring facility, the above-named patient has been **granted official permission** by the Federal Ministry of Health to seek medical care abroad for the above-mentioned condition, as the service is currently unavailable in Ethiopia.

In line with the medical board's recommendation, the patient will be accompanied

by:

- **Attendant (if applicable):** _____

Supporting Documents Attached:

- Certified medical board referral from the referring hospital
- Affidavit and relationship confirmation, authenticated by the Documents Authentication and Registration Service

Purpose of This Certificate

This certificate is issued for the purpose of facilitating:

- Visa and passport facilitation (where applicable) and immigration clearance
- Currency approval and foreign exchange processing via Ethiopia Bank.
- Coordination with the Ministry of Foreign Affairs and embassies
- Admission and coordination with the overseas treating hospital

Important Notes

- This certificate is valid only for the patient and named companions above
- It is non-transferable and any alteration or misuse will render it void
- Valid until: Six Months from date of issue

The Ministry of Health respectfully requests all relevant institutions to provide the necessary support and cooperation for the patient and companions during the treatment process.

Authorized by:
Name: _____
Title:
Organization: Ministry of Health, Ethiopia
Signature: _____
Official Seal

እዝል-4

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH - ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!

የምዝገባ ቁጥር

Reg.No

የኢትዮጵያፌዴራላዊዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የጤና ሚኒስቴር

MINISTRY OF HEALTH

ተገልጋይን ወደ ውጭ አገር ለህክምና የሚልክ ወኪል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

AGENT WHO SENDS PATIENTS ABROAD A PATIENT CERTIFICATE OF COMPETENCE

በጤና አገልግሎት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 አንቀፅ 11(3) የውጭ አገር ሕክምና አገልግሎት የሚያስፈልገውን ተገልጋይ ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ከውጭ ሕክምና ተቋም ጋር ለሚያገናኝ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የጤና ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት

ለ.....ተቋም ተገቢውን መስፈርት አሟልተው ስለተገኙ ሚኒስቴሩ በ.....መዝግቦ ይህን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጥቷል።

የኃላፊ ፊርማ .....ቀን/ወር/ዓ.ም.....

Under Article 11(3) of the Health Service Administration and Regulation Proclamation No. 1362/2017, the Ministry of Health is authorized to issue certificates of competence to entities that facilitate or provide services for patients seeking medical treatment abroad or connect them with foreign medical institutions.

Accordingly, the Ministry has verified that [Name of Institution/Individual] has fulfilled the requirements set by the Authority and has been duly registered and issued this Certificate of Competence.

Habtamu Hailemeskel

ማሳሰቢያ

ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፡-

- **በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡**
- **ስምና ፎቶግራፍ ከተገለፀው ሰው በስተቀር ሌላ አካል ሊገለገልበት አይገባም፡፡**
- **በማንኛውም ምክንያት ቢጠፋ ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታ አለብዎ፡፡**